የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር

አዲስ ነጋሪ ጋዜጣ

ADDIS NEGARI GAZETA

OF THE CITY GOVERNMENT OF ADDIS ABABA

ስምንተኛ ዓመት ቁጥር ፸
አዲስ አበባ መስከረም ፪ ቀን ፪ሺ፰ ዓ.ም

በአዲስ አበባ ከተማ
ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

Eighth year No.70
Addis Ababa September 13 , 2015

ማውጫ

የሸገር የብዙሀን ትራንስፖርት አገልግሎት ድርጅት ደንብ.....ገፅ ፩

CONTENTS

SHEGER MASS TRANSPORT SERVICE ENTERPRISE REGULATION.....Page 1

ደንብ ቁጥር ፸/፪ሺ፰
በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የሸገር የብዙሀን ትራንስፖርት አገልግሎት ድርጅትን ለማቋቋም የወጣ ደንብ

የአዲስ አበባ ከተማን ፈጣን ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ዕድገትን ለማሳካት ቀልጣፋና ተደራሽ የብዙሃን ትራንስፖርት አገልግሎት ሰጪ ተቋም ማቋቋም በማስፈለጉ፤

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የተቀናጀ የብዙሃን ትራንስፖርት አገልግሎት የሚሰጥ ድርጅት በማቋቋምና የተቋሙን አደረጃጀት በመወሰን ለከተማው ህብረተሰብ የተሻለና ውጤታማ የብዙሀን ትራንስፖርት አገልግሎት ማቅረብ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በተሻሻለው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁጥር ፫፻፷፩/፲፱፻፺፮ አንቀጽ ፳፫(፩)(ረ) በተሰጠው ስልጣን መሠረት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ካቢኔ ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

REGULATION No.70/2015
A REGULATION TO PROVIDE FOR THE ESTABLISHMENT OF SHEGER MASS TRANSPORT SERVICE ENTERPRISE OF ADDIS ABABA CITY GOVERNMENT

WHEREAS, it has been found necessary to establish an institution providing fast and accessible mass transport service to achieve the rapid economic and social growth of Addis Ababa City;

WHEREAS, it has been found necessary to provide better and effective mass transport service for the public of the City by establishing and defining organizational structure of an enterprise which provide integrated mass transport service;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 23(1) (f) of the Revised Charter of Addis Ababa City Government Proclamation No 361/2003 the City Cabinet has issued this Regulation as follows.

ክፍል አንድ
ጠቅላላ ድንጋጌዎች

፩. አጭር ርዕስ

ይህ ደንብ "የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የሸገር የብዙሀን ትራንስፖርት አገልግሎት ድርጅት ደንብ ቁጥር ፸/፪ሺ፰" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

፪. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፡-

፩. "ከተማ" ማለት የአዲስ አበባ ከተማ ነው፤

፪. "አስተዳደር" ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ነው፤

፫. "ቻርተር" ማለት የተሻሻለው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር ፫፻፷፩/፲፱፻፺፭ ነው፤

፬. "ቢሮ" ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር መንገድና ትራንስፖርት ቢሮ ነው፤

፭. "ባለስልጣን" ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የትራንስፖርት ባለስልጣን ነው፤

፮. "ደንብ" ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የልማት ድርጅቶች የሚመሩበትን ሁኔታ ለመወሰንና የተወሰኑ የልማት ድርጅቶችን ለማቋቋም የወጣው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ደንብ ቁጥር ፲፬/፲፱፻፺፭ ነው፤

፯. "ቦርድ" ማለት በቻርተሩ እና በዚህ ደንብ መሰረት የሚቋቋም የድርጅቱ አንድ የስልጣን አካል ነው፤

፰. "የብዙሃን ትራንስፖርት" ማለት አብዛኛውን የህብረተሰብ ክፍል እንዲያገለግል የሚደራጅ የትራንስፖርት አገልግሎት አሰጣጥ ሥርዓት ነው፤

PART ONE
General Provisions

1. Short Title

This Regulation may be cited as the "Addis Ababa City Government Sheger Mass Transport Service Enterprise Regulation No. 70/2015".

2. Definitions

Unless the context otherwise requires, in this Regulation:

1. **"City"** means the Addis Ababa City;
2. **"Government"** means the Addis Ababa City Government;
3. **"Charter"** means the Addis Ababa City Government Revised Charter Proclamation No. 361/2003;
4. **"Bureau"** means the Addis Ababa City Government Road and Transport Bureau;
5. **"Authority"** means the Addis Ababa City Government Transport Authority;
6. **"Regulation"** means the Addis Ababa City Government Regulation to Determine the Conditions Under which the Addis Ababa City Government Public Enterprises are to be Managed and to Establish Certain Public Enterprises Regulation No. 14/1999;
7. **"Board"** means an organ of the Enterprise to be established as per the Charter and this Regulation;
8. **"Mass Transport"** means a system organized to provide transport service for the majority section of the public;

፱. "ሰው" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

፲. በዚህ ደንብ ውስጥ በልዩ ሁኔታ ካልተገለፀ በስተቀር በወንድ ፆታ የተገለጹ አገላለጾች ለሴት ጸታም ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡

ክፍል ሁለት

ስለ ድርጅቱ መቋቋም፣ ዓላማ እና ሥልጣንና ተግባር

፫. መቋቋም

፩. ሸገር የብዙሀን ትራንስፖርት አገልግሎት ድርጅት (ከዚህ በኋላ "ድርጅት" እየተባለ የሚጠራ) የከተማ አስተዳደሩ የልማት ድርጅት ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል፤

፪. ድርጅቱ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የልማት ድርጅቶች የሚመሩበትን ሁኔታ ለመወሰንና የተወሰኑ የልማት ድርጅቶችን ለማቋቋም በወጣው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ደንብ ቁጥር ፲፬/፲፱፻፺፮ መሰረት ይተዳደራል፤

፫. የድርጅቱ ተጠሪነት ለቦርዱ ይሆናል፤ ሆኖም የዕለት ተዕለት ተግባራትን በተመለከተ በባለሥልጣኑ ይመራል፤

፬. የቻርተሩ አንቀጽ ፷ በድርጅቱ ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

፬. ዋና መስሪያ ቤት

የድርጅቱ ዋና መስሪያ ቤት በአዲስ አበባ ከተማ ማዕከል ሆኖ እንደ አስፈላጊነቱ በከተማው ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤቶች ሊኖሩ ይችላሉ፡፡

9. "Person" means natural or legal person;

10. Unless otherwise expressed, in this Regulation expressions stated in the masculine gender shall apply to the feminine gender.

PART TWO

Establishment, Objective, Power and Functions and Organization of the Enterprise

3. Establishment

1. Sheger Mass Transport Service Enterprise (hereinafter "Enterprise") is hereby established by this Regulation as a public enterprise of the City Government;

2. The Enterprise shall be governed by the Addis Ababa City Government Regulation to Determine the Conditions Under which the Addis Ababa City Government Public Enterprises are to be managed and to Establish Certain Public Enterprises Regulation No.14/1999;

3. The Enterprise shall be accountable to the Board and in the day-to-day activity shall be guided by the Authority;

4. Article 60 of the Charter shall be applicable to the Enterprise.

4. Head Office

The Enterprise shall have its head office in Addis Ababa City center and may have branch offices elsewhere in the City, as may be necessary.

፭. <u>አደረጃጀት</u>

ድርጅቱ የሚከተለዉ አደረጃጀት ይኖረዋል፡-

፩. የሥራ አመራር ቦርድ፤

፪. ዋና ሥራ አስኪያጅ፤

፫. ሁለት ምክትል ሥራ አስኪያጆች፤

፬. ሌሎች አስፈላጊ የሆኑ የሥራ ክፍሎችና ሠራተኞች፡፡

፮. <u>ዓላማ</u>

ድርጅቱ የተቋቋመባቸው ዓላማዎች የሚከተሉት ናቸው ፡-

፩. ለተማሪዎች ቀልጣፋና ተደራሽ መደበኛ የአዉ ቶብስ ትራንስፖርት አገልግሎት መስጠት፤

፪. ለከተማው ኅብረተሰብ የፈጣን አዉቶብስ ትራንስፖርት አገልግሎት መስጠት፤

፫. ከሌሎች የሕዝብ የትራንስፖርት አገልግሎት ሰጪዎችና ባለድርሻ አካላት ጋር በሚጣጣም ሁኔታ የተቀናጀ የትራንስፖርት አገልግሎት መስጠት፡፡

፯. <u>ካፒታል</u>

ለድርጅቱ የተፈቀደው ካፒታል ብር ፪ ቢሊየን ፮፻፵፪ ሚሊየን (ሁለት ቢሊየን ስድስት መቶ አርባ ሁለት ሚሊየን ብር) ሲሆን ከዚህ ውስጥ ብር ፯፻፴፩ ሚሊየን ፫፻፵፩ ሺህ ፭፻፷፬ (ሰባት መቶ ሰላሳ አንድ ሚሊየን ሶስት መቶ አርባ አንድ ሺህ አምስት መቶ ስልሳ አራት ብር) በአይነት ተከፍሏል፡፡

፰. <u>የድርጅቱ ስልጣንና ተግባራት</u>

ድርጅቱ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

፩. የብዙሀን ትራንስፖርት በህዝብ ዘንድ ተፈላጊና ተመራጭ እንዲሆን ይሰራል፤

5. <u>Organizational Structure</u>

The Enterprise shall have the following organizational structure:

1. Management Board;
2. Chief Manager;
3. Two Deputy Managers;
4. Other necessary departments and staffs.

6. <u>Objective</u>

The objectives for which the Enterprise is established are:

1. to provide fast and accessible formal bus transport service for the students;
2. to provide fast bus transport service to the public of the City;
3. to provide integrated transport service corresponding with other public transport providers and stakeholders.

7. <u>Capital</u>

The authorized capital of the Enterprise is Birr 2,642,000,000.00 (Two Billion Six Hundred Forty Two Million Birr) of which Birr 731,341,564.00 (Seven Hundred Thirty One Million Three Hundred Forty One Thousand Five Hundred Sixty Four Birr) is paid up in kind.

8. <u>Powers and Duties of the Enterprise</u>

The Enterprise shall have the following powers and duties:

1. work to make mass transport demanded and preferred by the public;

፪. መደበኛ የከተማ አዉቶብሶችና የተማሪዎች አዉቶብሶች በመጠቀም በተመጣጣኝ ዋጋ ለኅብረተሰቡ የፈጣን አዉቶብስና የመደበኛ አዉቶብስ የትራንስፖርት አገልግሎት ያቀርባል፤

2 provide express bus and formal bus transport service for the public at fair price by using formal buses and school buses;

፫. ሁሉንም የኅብረተሰብ ክፍል በተለይም ተማሪዎችን፣ አረጋዊያንን፣ አካል ጉዳተኞችን ህጻናትን ንና ነፍሰጡሮችን እኩል ተጠቃሚ የሚያደርግ ምቹና አስተማማኝ የብዙሃን ትራንስፖርት አገልግሎት ይሰጣል፤

3 provide comfortable and safe mass public transport which makes equally benefiting all members of the public especially students, elderly, persons with disability, children and expectant mothers;

፬. አገልግሎት አሰጣጡ በተገቢው የቴክኖሎጂ አውታሮች የታገዘ፣ ተመራጭ፣ ቀልጣፋ፣ ተደራሽና አስተማማኝ እንዲሆን ያደርጋል፤

4 make its service delivery assisted with suitable technology infrastructure, demanded, efficient, accessible and safe;

፭. ከባለሥልጣኑ በሚሰጠዉ የአገልግሎት ክፍያ መጠን፣ የመስመር ድልድል እና የጊዜ ሰሌዳ መሠረት አገልግሎት ይሰጣል፤

5 provide service based on the tariffs, route arrangement and service schedule set by the Authority;

፮. ከባለሥልጣኑ በሚሰጥ አቅጣጫ መሠረት ለብዙሃን ትራንስፖርት አገልግሎት የትኬት ሽያጭ አሰራር ይዘረጋል፣ ትኬት ይሸጣል፣ ገቢ ይሰበስባል፤

6 set up ticketing and selling system for mass transport service based on direction given by the Authority, sell same and collect income;

፯. አዉቶብሶቹ በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የተደገፈ የተሽከርካሪ ምርመራ፣ ቀላል ጥገና እና የእድሳት አገ ልግሎት እንዲያገኙ ያደርጋል፤

7 make the buses technologically assisted vehicle inspection, simple repair and maintenance service;

፰. የትራንስፖርት አገልግሎት አሰጣጥ ላይ የተሟላ መረጃ ለህብረተሰቡ ተደራሽ ያደርጋል፤

8 make the information accessible for the public on transport service delivery;

፱. ለአዉቶብሶቹ ምቹ መንገድ እና የተለየ የአዉቶብስ የጉዞ መስመር እንዲኖር ከባለድርሻ አካላት ጋር በጋራ ይሰራል፤

9 work in collaboration with stakeholders for the existence of conducive road for the buses and bus lane;

፲. ለድርጅቱ የሚያስፈልጉ ዴፖ፣ የተርሚናል፣ የጥገና እና የመሳሰሉት መሰረተ ልማቶች እንዲሚሉ ከባለሥልጣኑ ጋር በጋራ ይሰራል፤

10 work in collaboration with the authority towards fulfillment of depots, terminals, repair and other infrastructure necessary for the Enterprise;

፲፩. በቦርዱ ውሳኔ መሰረት አዉቶብሶችን ይገዛል፣ በሥራ ላይ ያዉላል ይሸጣል፤

11 buy, use and sell buses in accordance with the decision of the Board;

፲፪. የትራንስፖርት ባለስልጣን በሚያወጣው ስታንዳርድ መሰረት የትራንስፖርት አገልግሎቱ የጥራት ደረጃውን የጠበቀ መሆኑን ያረጋግጣል፤

፲፫. በትራንስፖርት አገልግሎት ዘርፍ ከተሰማሩ እና ጠቃሚ ልምድ ካላቸው የብዙሃን ትራንስፖርት ተቋማት ጋር በትብብር ይሰራል፤

፲፬. የተሰጠውን ተልዕኮ ሊያሳኩ የሚችሉ በስራ አስፈፃሚ ወይም በቦርዱ ተለይተው የሚሰጡ ትን ሌሎች ተግባሮችን ያከናውናል፤

፲፭. የንብረት ባለቤት ይሆናል፣ ውል ይዋዋላል፣ በራሱ ስም ይከሳል፣ ይከሰሳል፤

፲፮. ዓላማዉን ከግብ ለማድረስ የሚረዱ ሌሎች ተግባራትን ይፈጽማል።

፱. <u>የሥራ አመራር ቦርዱ ስልጣንና ተግባር</u>

የሥራ አመራር ቦርዱ የሚመለከታቸውን የመን ግስት ከፍተኛ አመራሮችና ባለድርሻ አካላት ያካተተ ሆኖ የሚከተሉት ሰልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፦

፩. የድርጅቱን አጠቃላይ እንቅስቃሴና የሥራ አፈጻጸም ይቆጣጠራል፤

፪. ለድርጅቱ ዋና ሥራ አስኪያጅ ተጠሪ የሆኑ የሥራ ኃላፊዎችን ቅጥር፣ ምደባና ስንብት ይወስናል፤

፫. የድርጅቱን የሥራ ፕሮግራም፣ በጀትና ውስጠ ደንቦችን ያፀድቃል፣ አፈጻፀማቸውንም ይከታተላል፤

፬. በዋና ሥራ አስኪያጅ ሪፖርት መነሻ የድርጅቱን የበጀትና የሥራ ዕቅድ አፈጻጸም ይገመግማል፣ አቅጣጫ ይሰጣል፤

12. ensure that its transport service is as per the standard issued by the Transport Authority;

13. work in collaboration with those who engaged in transport service sector and with institutions which has good practice in mass transport;

14. discharge other duties which may be specifically entrusted to it by the Executive Committee or the Board in order to achieve its mission;

15. own property, enter into contract, sue and be sued in its own name;

16. Perform such other activities that help to achieve its objectives.

9. <u>Power and Function of the Management Board</u>

The Board, being extracted from the concerned government officials and stakeholders, shall have the following powers and functions:

1. Generally follow up activities of the Enterprise;
2. Decide on the employment, deployment and dismissal of officials of the Enterprise accountable to the chief Manager;
3. Approve the activity program, budget, and internal regulations of the Enterprise; follow up implementation of same;
4. Evaluate and give direction on the budget and activity plan implementation of the Enterprise based on the report of the chief Manager;

፭. ድርጅቱን ለማሳደግ የሚያስፈልጉ የፖሊሲ ጥያቄዎችና ሌሎች የአሠራር ደንብና መመሪያ ዎችን በመርመር ለውሳኔ ለሚመለከተው የመንግሥት አካል ያቀርባል፤

፮. ለድርጅቱ የሚያስፈልገውን በጀትና የሥራ ማስኬጃ ያጸድቃል፤

፯. የድርጅትን የረዥም ጊዜ ብድሮችና ክሬዲቶች ያፀድቃል፤

፰. በከተማው ካቢኔ በሚወጣ መመሪያ መሠረት የገንዘብ ወጪ ይፈቅዳል፣ በድርጅቱ ሕልውና ላይ ወሳኝነት የሌለውን የቋሚ ንብረቶች ሽያጭ ያፀድቃል፤

፱. የድርጅቱ ሂሣቦችና ንብረቶች በአግባቡ መያዛ ቸውን ያረጋግጣል፤

፲. የውጭ ኦዲተሮችን ይሰይማል፤ ለተሰየሙ ኦዲተሮች የድርጅቱ የሂሣብ መዝገቦች መቅረባ ቸውን ያረጋግጣል፤

፲፩. የድርጅቱን የሂሳብ ሪፖርትና የውጪ ኦዲተር ሪፖርት ያፀድቃል፤

፲፪. የድርጅቱ ካፒታል እንዲጨመር፣ ወይም እንዲ ቀንስ ለከተማው ካቢኔ ሃሳብ ያቀርባል፤

፲፫. በከተማው ካቢኔ በሚወሰነው ደረጃ መሠረት የዋና ሥራ አስኪያጅን የደመወዝ ጣሪያ ተከትሎ የበታች ኃላፊዎችንና ሠራተኞችን የደመወዝ እርከንና የድርጅቱን አደረጃጀት ይወስናል፣ ተግባራዊ መሆኑንም ያረጋግጣል፤

፲፬. አፈፃፀም ሪፖርት ለሚመለከተው የመንግሥት አካል ያቀርባል።

5. Evaluate and submit for decision to the concerned Government organ policy issues necessary for growth of the enterprise;

6. Approve the budget necessary to undertake activities of the Enterprise;

7. Approve long term borrowings and credits of the Enterprise;

8. Order expenditure based on directive issued by the Cabinet; approve sale of properties indifferent to the Enterprise;

9. Ensure that the accounts and properties of the Enterprise are properly kept;

10. Nominate external auditors for the Enterprise; ensure that the financial documents are presented to the auditors;

11. Approve the account report and report of external auditors of the Enterprise;

12. Submit recommendation to the Cabinet on the increase or decrease of capital of the Enterprise;

13. Decide on the salary scale of the lower officials and employees of the Enterprise following that of the chief Manager and based on the level determined by the Cabinet; follow up implementation of same;

14. Submit report about performance of the Enterprise to the concerned government organ.

፲. የድርጅቱ ዋና ሥራ አስኪያጅ ስልጣንና ተግባር

የድርጅቱ ዋና ሥራ አስኪያጅ ተጠሪነቱ ለድርጅቱ ሥራ አመራር ቦርድ ሲሆን በቀን ተቀን ተግባሩ ተጠሪነቱ ለትራንስፖርት ባለስልጣን በመሆን የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

፩. የድርጅቱን ሥራ በበላይነት ያቅዳል፣ ያደራጃል፣ ይመራል፣ ያስተዳድራል፣ ይቆጣጠራል፣ አፈጻጸሙን ይገመግማል፣

፪. ድርጅቱ ከሦስተኛ ወገኖች ጋር በሚያደርገው ማናቸዉም ስምምነቶች ድርጅቱን በመወከል ይፈራረማል፣ ውሎቹና ስምምነቶቹ ተግባራዊ መሆናቸውን ይከታተላል፣

፫. ለእርሱ ተጠሪ የሆኑ የሥራ ኃላፊዎች ለቦርዱ እያቀረበ ያጸድቃል፣ የስራ እንቅስቃሴያቸዉን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣

፬. ድርጅቱን ውጤታማ፣ ተወዳዳሪና ትርፋማ ሊያደርጉ በሚያስችሉ ስትራቴጂያዊ ጉዳዮች ላይ ትኩረት በማድረግ የአሰራር ሥርዓቶችን ይዘረጋል፣

፭. ሌሎች ሠራተኞችን ይቀጥራል፣ ይመድባል፣ ተግባራቸውን ይወስናል፣

፮. የድርጅቱን ፋይናንስ ያንቀሳቅሳል፣ ወጭዎችን ይፈቅዳል፣ ያጸድቃል፣

፯. የፋይናንስ እና ንብረት አያያዝና አጠቃቀም በመመሪያው መሠረት መተግበሩን ያረጋግጣል፣

፰. የድርጅቱን የሥራ ፕሮግራምና በጀት እንዲሁም ደንብና መመሪያ አዘጋጅቶ ለቦርዱ ያቀርባል፣ ሲፈቀድም ሥራ ላይ ያውላል፣

፱. ዉሳኔ የሚሹ ጉዳዩችን ለቦርዱ ያቀርባል፣ የቦርዱን ውሣኔዎች ይፈጽማል፣ ያስፈጽማል፣

10. Powers and Functions of the chief Manager

The chief Manager, being accountable to the Management Board and guided by the Authority in its day-to-day activity, shall have the following powers and functions:

1. Superiorly plan, organize, direct, administer, supervise activities of the Enterprise; evaluate the implementation thereof;
2. Sign every agreement Enterprise, enters with third parties; follow up implementation of contracts and agreements;
3. Recommend the nomination of officials accountable to him for approval of the Board; follow up and supervise their activities;
4. Install working procedures focusing on strategic issues that enable the Enterprise effective, competitive and profitable;
5. Employ, deploy the staff of the Enterprise and determine their respective function;
6. Permit, approve expenditure and manage account of the Enterprise;
7. Ensure that the management and utilization of finance and property of the Enterprise is implemented in accordance with the directive;
8. Prepare and submit the activity and budget plan, internal regulation and directive to the Board; implement same upon approval;
9. Submit matters demanding decision to the Board; execute and cause the execution of decisions of the Board;

፲. በሥራው ሂደት ላይ የሚመክርና በዕቅዶችና ውሣኔዎች ላይ የሚወያይ የማኔጅመንት ኮሚቴ ያቋቁማል፣ ስብሰባውን ይመራል፣ ውሳኔዎችን ያስተላልፋል፣

፲፩. ቦርዱ የሚሰጠውን ሌሎች ተጨማሪ ሥራዎች ያከናውናል፣

፲፪. የድርጅቱን ሥራ አፈጻጸም በተመለከተ ለቦርዱና ለትራንስፖርት ባለሥልጣን ወቅታዊ ሪፖርት ያቀርባል፣ በሚሠጠውም ግብረ-መል ስና አቅጣጫ መሠረት ተግቢውን ይፈጽማል፡፡

፲፩. <u>የምክትል ሥራ አስኪያጅ ስልጣንና ተግባራት</u>

ምክትል ሥራ አስኪያጁ ተጠሪነቱ ለዋና ሥራ አስኪያጁ ሆኖ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባር ይኖረዋል፡-

፩. የድርጅቱን የሥራና የበጀት ዕቅድ በማዘ ጋጀትና በመተግበር ዋና ሥራ አስኪያጁን ያግዛል፣

፪. የድርጅቱ ዋና ሥራ አስኪያጅ በሌለበት በእርሱ ተለይቶ የተወከለው ምክትል ዋና ሥራ አስኪያጅ እሱን ተክቶ ይሰራል፣

፫. የተመደበበትን የሥራ ክፍል የመምራት ሥራ ይሠራል፣

፬. የድርጅቱን ግብና ዓላማ ለማሳካት በዋና ሥራ አስኪያጁ የሚሰጡ ሌሎች ተግባራትን ያከና ውናል፡፡

፲፪. <u>የዋናና የምክትል ሥራ አስኪያጆች አሿሿም</u>

የድርጅቱ ዋናና ምክትል ሥራ አስኪያጆች በከተማዉ ከንቲባው ይሾማሉ፡፡

10. Establish management committee that discusses on the activities, plans and decisions; chair meetings of the committee;

11. Perform such other activities designated by the Board;

12. Submit timely report to the Board and the Authority regarding performance of the Enterprise; properly execute based on the feedback and direction given thereof.

11. <u>Power and Function of the Deputy Manager</u>

The Deputy Manager, being accountable to the chief Manager, shall have the following powers and functions:

1. Support the chief Manager in the preparation and implementation of the activity and budget plan of the Enterprise;
2. Represent the chief Manager in his absence, where specifically delegated;
3. Perform activities of managing the department to which he is assigned;
4. Perform such other activities designated by the chief Manager with the view to achieve objectives of the Enterprise.

12. <u>Appointment of the Chief and Deputy Managers</u>

The Chief and Deputy Managers of the Enterprise shall be appointed by the Mayor of the City.

፲፫. ኃላፊነት

ድርጅቱ ካለው ጠቅላላ ንብረት በላይ በዕዳ ተጠያቂ አይሆንም፡፡

፲፬. ድርጅቱ የሚቆይበት ጊዜ

ድርጅቱ ላልተወሰነ ጊዜ ይቆያል፡፡

ክፍል ሦስት
ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

፲፭. ይህ ደንብ ከመውጣቱ በፊት ስለተደረጉ እንቅስቃሴዎች

ድርጅቱ ይህ ደንብ ከመውጣቱ በፊት ያከናወናቸው ተግባራት በዚህ ደንብ ሕጋዊ እውቅና ተሰጥቷቸዋል፡፡

፲፮. የመተባበር ግዴታ

ማንኛውም ሰው ይህን ደንብ የማክበርና የማስ ከበር ግዴታ አለበት፡፡

፲፯. መመሪያ የማውጣት ሥልጣን

ይህን ደንብ ለማስፈፀም የሚያስፈልጉ መመሪያ ዎችን ቢሮዉ ሊያወጣ ይችላል፡፡

፲፰. ተፈጻሚነት የሌላቸዉ ሕጎች

ከዚህ ደንብ ጋር የሚቃረን ማንኛዉም ደንብ፣ መመሪያ ወይም ልማዳዊ አሠራር በዚህ ደንብ በተካተቱ ጉዳዮችን በተመለከተ ተፈጻሚነት አይኖረዉም፡፡

13. Liability

The Enterprise shall not be liable beyond its total asset.

14. Duration of the Enterprise

The Enterprise is established for an indefinite duration.

PART THREE
Miscellaneous provisions

15. Undertakings Carried Out before the Issuance of this Regulation

The undertakings which have been carried out by the Enterprise prior to this Regulation are hereby recognized by this Regulation as lawful and valid.

16. Duty to Cooperate

Any person shall be duty bound to cooperate for the implementation of this Regulation.

17. Power to Issue Directives

The Bureau may issue directives necessary for the proper implementation of this Regulation.

18. Inapplicable Laws

No Regulation, directive or customary practice shall, in so far as it is inconsistent with this Regulation, have effect in respect of matters provided for in this Regulation.

፲፱. ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ ደንብ ከመስከረም ፪ ቀን ፪ሺ፰ ጀምሮ የፀና ይሆናል።

አዲስ አበባ

ጳጉሜ ፭ ቀን ፪ሺ፯ ዓ.ም

ድሪባ ኩማ

የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ

19. Effective Date

This Regulation shall enter into force as of 13th day of September 2015.

Done at Addis Ababa,

This 11th Day of September, 2015

Diriba Kuma

Mayor of Addis Ababa City